# “ቴዲ አሁንስ የቀረለት አልመሰለኝም!”

*ዳኛ ወልደሚካኤል መሸሻ*

ወያኔ-ኢህአዴግ ለራሱ በአደገኛነቱ አንድ ጊዜ በጥርሱ ከነከሰው፣ በዚህም በዚያም አድርጎ መቦጫጨቁን አይለቅም። ማንን ፈርቶ! ለጊዜው ሁሉም በጁ፣ ሁሉም በደጁ አይደል? መቼም አበው ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል ይሉ የለም። እውነታቸው ነው። ዛሬ ሁሉም አልጋባልጋ የሆነላቸው፣ ያ ቀን እስከሚመጣ ድረስ ነጋም ዛሬ ይመስላቸዋል።

ባለፈው “አሁንም ፍትህን ለይቅርታ!” በተሰኘው ርዕስ በቴዎድሮስ ላይ የቀረበውን ክስና ማስረጃ ላይ የራሴን ትንተናና መደምደሚያ ለመስጠት ሞክሬ እንደነበር ይታወሳል።

አሁን ወደዚያው እንዳለ ልመለስ ሳይሆን፣ ብዙዎች እንደሚሉትና እኔም እንደምስማማው ቴዲ ለዘብጥያ የተዳረገው፣ የቀረበበት ወንጀል ፈጽሞ ሳይሆን፣ የወያኔ-ኢህአዴግ የሚሰራቸውን ሕዝቡን በጎሳና በዘር ከፋፍሎ አገርን መበታተኑን ቆም አድርጎ በማሰብ ከሕዝቡ ጋር ሰላም ፈጥሮ አገራችን ወደነበረችበት ወደ አንድነቷ እንድትመለስ በዝማሬው፣ ለዛ ባለው የሙዚቃ ቅላጼው መንገሩን በመቀጠሉ ነው። ታዲያ ይህ አካሄዱ ለሕዝብ፣ ስለሕዝብ በሕዝብ ስም እንደመሆኑ መጠን የሰላማዊ ትግል መንገድ ይመስለኛል። እርቅና ይቅርባይነትን በተለይ መንግስት እንዲቀበልና አገራችን ካንጃበባት አደጋ ለመታደግ ይመስለኛል። ግን ግና ይህ እንደኃጢአት ተቆጠረና በቅንብር መረብ ለቴዲ ተዘጋጀለት እንደተለመደው። የወጣትነት እንቅስቃሴውን ሽባ ለማድረግ፣ የወጣትነት ወኔውን ለማኮላሸት። ለነገሩ ነገሩ ነው እንጂ ጩቤ ሰውን አይጎዳም ተብሎአል። አላወቁትም እንጂ ቴዲ ለብቻው አይደለም ከሕዝቡ ጋር እንጂ።

እናም፣ በዚያ አነስተኛ ጽሑፍ ላይ ከጠቃቀስኳቸው ሌሎችን ትቼ በተለይም በምስክሮች የተነገረውን የሟቹን ሬሳና አወዳደቁን በሚመለከት ያሰፈርኩት አሁን በቅርብ ከቀረበው የሬሳ ምርመራ ሰነድ ጋር በአጭሩ የምችለውን እላለሁ። የዓይን ምስክር ሆኖ የቀረበው አንደኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር፣ ሟቹ ደጉ ይበልጣል በአስፋልቱ ላይ ወድቆ ባለበት ላይ ያች እንደአነጋገሩ በጣም ፍጥነት የነበራት መኪና ገጭታው ሄዳለች፣ ከሁለተኛው ምስክር ጋር ተመልሰው ሲመለከቱትም ትንፋሽ እንደነበረውና ከአምስት ደቂቃ በኋላ ነፍሱ እንደወጣች ነው ለፍርድ ቤቱ ያስረዳው። የሬሳ ፕላን አንሺው ትራፊክ ፖሊስ ፓላኑን በሚያነሳበት ወቅት የነበረውን አቅጣጫ ሲገልጽ፣ የሟቹ ሬሳ ጭንቅላት ወደ ካዛንችስ እግሩ ደግሞ ወደ አራት ኪሎ እንደነበረ ነው። በወቅቱ እነዚህን አመሰካከሮችን ተንተርሼ፣ በትክክል ሰውየው መኪናው ከመድረሱ በፊት ወድቆ ከሆነ መባል ያለበት ገጭቶ ሄደ ሳይሆን፣ ጨፍልቆት ሄደ ወይም ነዳበት ነው። እንዲህ ከሆነም የፕላን ምስክሩ እንዳስረዳው የሟቹ የውሰውነት ክፍሎቹ እንዳሉ ሆነው ራሱ እንደዚያ እግሩ እንደዚህ ተብሎ አቅጣጫው ሊነገር አይቻልም ነበር። ተራፊው የሰውነቱ ክፍል ወዲያና ወዲህ ተበታትኖ ይገኛል እንጂ ተገጭቶ እንደወደቀ ሰው ሰውነቱ እንዳለ ማግኘት ፍጹም አይቻልም። ግን እንደተጠቀሰው ፕላን አንሺው ምስክር የሟቹ ሰውነት ሳይበታተን ባለበት ነው ያገኘው። በመሆኑም እንደ ክሱ አመሰራረትና እንደዚህ ማስረጃ አገላለጽ መሰረት የቴዲ መኪና የተባለውን ሰው አልገጨውም ወይም አልነካውም ማለት ነው። ይህ ደግሞ ክሱን ምክንያታዊ በሆነ ጥርጣሬ ውስጥ ይከተዋል። በመሆኑም፣ ዐቃቤ ሕግ ክሱን ምክንያታው ከሆነው ጥርጣሬ ውጭ አላስረዳምና ይኸው ብቻ በራሱ ፍ/ቤቱ ቴዲን ከክሱ በነጻ ሊያሰናብት ከሚያበቃው አንዱ ነው ብዬ እንደነበርም ይታወሳል።

ሰኔ 27 ቀን 2000 ዓ.ም የቴዲ ጉዳይ እልባት ያገኛል ተብሎ በቴዲም በታዳሚዎች ኢትዮጵያዊያን ሕዝብ ዘንድ በከፍተኛ ጉጉት ይጠበቅ እንደነበር ይታወቃል። በነጻ ይለቀቃል የሚል ጉጉት። ግን አሁንም ለሌላ ምርመራ መቀጠሩን ነው በዕለተ ቀኑ የሰማነው። ለእኔ ግን አልደነቀኝም፤ እጠብቀው ስለነበር። ወያኔ ጠንካራ ተቀናቀኝ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች እንቅስቃሴ ለማቆም ወይም ለማስወገድ ሲፈልግ ልክ እንደ ቴዲ ዓይነት የሆነ ወንጀል ይቀምርና ወደ ከርቸሌ ያወርዳል። የተዘጋጀው ማስረጃ በመጠኑም ቢሆን የማያስኬደው ከሆነ በቀጠሮች በእስር ቤት እንዲማቅቁ፣ እንዲጉላሉ ያደርጋልና፤ ያስደርጋልና። እኔን ያስገረመኝ በግንቦት 27 ቀን 2000 ዓ.ም ቀጠሮው በዐቃቤ ሕግ የቀረበው የሬሳ ምርመራ ማስረጃ ፦

1. ኦርጅናል ሳይሆን፣ ቅጂ መሆኑን፣
2. የመርማሪው ስም ኢሳያስ ከመባል በስተቀር ያባቱ ስም ያለመጠቀሱን፣
3. የዶ/ር ፍሪማ የሌለበት መሆኑን፣
4. አስከሬኑ ቀና ተደርጎ ፎቶግራፍ የተነሳበት መሆኑን ያመላከተ ሆኖ መገኘቱን ከዌብሳይቶች ለማየት ተችሎ ግን ይህ ቁልጭ ያለ የቅጥፈት ማስረጃ ቀርቦ እያለ ፍ/ቤቱ መዝገቡን ለብይን ማሳደር ሲገባው፣ ኦርጅናል ማስረጃ ዐቃቤን ካላቀረበ በሚል ኦርጅናል ማስረጃ እንዲያቀርብ ለሰኔ 27 ቀን 2000 ዓ.ም ቀጠሮ መስጠቱ፣ እና እንደገናም ይኸው ቀነ-ቀጠሮ ሰኔ 27 ቀን ደረሶ ኦሪጅናል ነው የተባለው ማስረጃ ቀረበ በዐቃቤ ሕጉ። ከኢትዮጵያዛሬ ዌብሳይት ላይ እንደተመለከትሁት የቀረበው የሬሳ ምርመራ ሰነድ ሟቹ ወደ ሆስፒታሉ ገብቶ የሞተው ጥቅምት 23 ቀን 1999 ዓ.ም ነው፣ የተመረመረው ደግሞ ጥቅምት 24 ቀን 1999 ዓ.ም ነው ይላል። ሆኖም ግን ፍ/ቤቱ ቢያንስ ለአዳሪ መዝገቡን መቅጠር ሲኖርበት ለሳምንት መቅጠሩ ነው።

በመሠረቱ የተከሠሰ ሰው እስካልተፈረደበት ድረስ እንደንጹህ ሰው እንደሚቆጠር ሕገመንግሥቱም ሆነ ወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ይደነግጋሉ። ይህ አለም-አቀፍ የሕግና ሕጋዊነት መርህ ነው። በመሆኑም፣ ተጠርጥሮ በቁጥጥር ሥር የዋለ ሰው በማናቸውም መልክ ጉዳት እንዳይደርስበት ጉዳዩን የያዘው ፍ/ቤት ሕጉ የሚጠይቀውን ጥንቃቄ ሊያደርግለት ይገባል። የጊዜ ቀጠሮውን እንተወው ብንል፣ ማስረጃዎቹ ከተሰሙ በኋላ እንኳንስ ለሕግ ሰው፣ እንኳንስ ፊደል ለቆጠረ ቀርቶ ለመሃይሙም የቴዲ ጉዳይ ቁልጭ ብሎ የሚታይ ነበር። በተለይም የሬሳ ምርመራ ሰነድ ስንመለከት፣ ከላይ በአጭሩ እንዳስቀመጥሁት የመዝገቡና የጉዳዩ ባለቤት ዐቃቤ ሕግ፣ ያውም የሬሳ ምርመራ ሰነድን የሚያህል ኮፒ ሲያቀርብ ዋናውን ለማቅረብ ያለመቻሉን ወዲያዉኑ ፍ/ቤቱ ተገንዝቦ ወደ ብይን መሄድ ነበረበት። በግድያና በግጭት ሰው በሞተ ጊዜ የሬሳ ምርመራ ሰነድ እንደ ዋና ማስረጃ ነው የሚታየው። የአገዳደሉን ሁኔታና አማሟቱን ያስረዳልና። ይህንኑ ዐቃቤ ሕጋዊያን ጠንቅቀው ያውቃሉ። ዐቃቤ ሕጉ በዚያ ቀጠሮ ተቸግሮ ነው ያንን የኮፒ ማስረጃ ያቀረበው። ዋናውን ሊያገኝ አልቻለም ማለት ነው። ይህም ወዶ አይመስለኝም። በአገራችን የሬሳ ምርመራን(post-mortem, autospy) ሥራ የሚያከናውኑ ባለሙያዎች የሚገኙት በምኒልክ ሆስፒታል ብቻ ሲሆን፣ አሁን ካልተጨመሩ በስተቀር እስከማውቀው ድረስ ሁለት ሐኪሞች ብቻ ነበሩ። በእውነት ትንሽ በኮሚሽኑ ምርመራ ወቅት ወደ መጀመሪያው አከባቢ ዋና ሃላፊዎቹ ለማንገራገር ከመሞከራቸው በስተቀር፣ ከሞላ ጎደል ሆስፒታሉ ጠንካራ ሐኪሞች ያሉበት ነው። በዚህ ጉዳይ በማስረጃው ማጭበርበር ላይ የሬሳ ምርመራ ዶክተሮች ሊተበበሩ እንዳልቻሉ ነው የገባኝ። ስለዚህ ነው ዐቃቤ ሕጉ ከየትም የተዘጋጀ የኮፒ ማስረጃ ያቀረበው በመጀመሪያው።

የተቸገረው ዐቃቤ ሕግ በቀረበው ወስንልኝ፣ እባክህን ገላግለኝ እያለው ግን ፍ/ቤቱ የለም ከየትም ወልደህ ዋናውን የምርመራ ሰነድ አቅርብ ስለው፣ የሚይዘውን የሚጨብጠውን አጥቶ ይኸውና ቅዝምዝም ወዲያ ፍየል ወዲህ ዓይነት ማስረጃ ይዞ ቀረበ። አሁንም ሐኪሞቹ የተበገሩ አልመሰለኝም እንደኔ ግምት። እንዲህ ነው ቃል! እንዲህ ነው ዶ/ር! እንዲህ ነው ሐኪም አልሁ በሆዴ ዜናውን እንዳነበብሁ። መቼም የእናት ሆድ ዥጉርጉር ነው ይባል የለ። እንደፖሊስ ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተሮች ዓይነት አሳፋሪ ሐኪሞች እንዳሉን ሁሉ፣ የምኒልክ ሆስፒታል የአውቶፕስይ ሐኪሞች ዓይነት ለቃላቸውና ለሕሊናቸው የቆሙ አሉን ማለት ነው። ሰዎች ቢያንስ በግለስብ ደረጃም ቢሆን ሕልናን ላለመሸጥ የሚያደርጉት አስተዋጽኦ በሕብረተሰቡ ዘንድ በምሳሌነቱ ከፍተኛ የሆነ ቦታ አለው። እናም፣ ኮርቼባቸዋለሁ።

## አሁን ደግሞ ዳኛው ምን ያደርግ ይሆን?

ይህ ጥያቄ ቴዲ ተፈቶ ለማየት ለሚጓጓው የኢትዮጵያን ዘንድ የሚጉላላ ጥያቄ ይመስለኛል። ቀደም ብዬ እንደገለጽሁት ቴዲ በብይን መለቀቅ የነበረበት የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተሰምተው እንደተጠናቀቁ፣ በተለይም ደግሞ እንደዚያ የሬሳ ምርመራው ውጤት ሰነድ ኮፒው በቀረበ ጊዜ ነበር። ዐቃቤ ሕጉ በቀረበው ማስረጃ፣ በቀረበው ሁኔታ ይወሰንልኝ ብሎ ለፍ/ቤቱ ሲያመለክት ሌላ ማስረጃ የለኝም። ያገኘሁት ይህን ብቻ ነው ማለቱ ነበር። ግን ዳኛው ልዑል ነውና፣ ዐቃቤ ሕግም ጭምር ሆኖ የሚሰራ ነውና፣ ኦርጅናል ወልደህም ቢሆን አምጣ በሚል ለዚያውም ከወር በላይ ለሆነ ጊዜ ቀጠረው። ግን ያልታሳካለት ዐቃቤ ሕግ በአለቆቹ አማካይነት የተሰጠውን፣ ከክሱ ጋር የማይገናኝ የምርመራ ማስረጃ ይዞ ቀረበ። እውነት ስለእውነት ምሎ ለገባው የዳኝነት ቃል ቢገዛ ኖሮ፣ ለሕሊናው ያለአድሎ የሚሰራ ቢሆን ኖሮ፣ ዳኛው በአዳሪ ቀጥሮ መዝገቡን በሰራው ነበር። ግን ለሳምንት ቀጠረው። ለምን? እንደሚመስለኝ በነዚህ ቀናት ውስጥ ሌላ ከክሱ ጋር የሚስማማ ማስረጃ በፎርጀሪ ተሰርቶለት እስኪቀርብ ይሆናል የሚልም ጥርጣሬ አድሮብኛል። ዐቃቤ ሕጉ ትክክለኛው ማስረጃ ማለትም ኦርጅናሉ ተገኝቶአልና ፍ/ቤቱ ይቀበለኝ ብሎ ከቀነ-ውሳኔ በፊት ለፍ/ቤቱ ጥያቄ ማቅረብ ይችላልና። ፍ/ቤቱም ካመነበት ምርመራውን ያቆምና ጥያቄውን ሊቀበለው ይችላልና። እንዲህም ከተፈጸመ ደግሞ፣ ልዑል ዓይኑን ጨፍኖ የሚቀበል ይመስለኛል። ለንዲህ ዓይነት ጉዳይ የቆመ፣ ያለ ዳኛ ነውና። የመንግሥት ጥረት ከመጀመሪያውኑ ቴዲን በፍትህ ስም ይቅርታ ለማስጠየቅ፣ ብሎም በግሉ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ውጭ ለማስደረግ ነው። ታዲያ እንግዲህ የትያትሩን መጨረሻ ዐርብ ሐምሌ 4 ቀን 2000 እናይ ይሆን? ሁላችን በፀሎት እንጠብቅ!!